02

አንደኛ ዓመት ቁጥር 3
1st Year No. 3

ባሕር ዳር ሰኔ 18 ቀን 1985
Bahir Dar 25th June 1993

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
የክልል 3 መስተዳድር
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
OF THE GOVERNMENT OF REG. 3
IN THE TRANSITIONAL GOVT. OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በክልል 3 መስተዳድር ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ. ሣ. ቁ. 312 P. O. BOX 312

ማ ው ጫ

ዐዋጅ ቁጥር 3/1985 ዓ/ም
የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር
ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ዐዋጅ ገጽ 12

CONTENT

PROCLAMATION No. 3/1993
A Proclamation to Establish the Courts of the Transitional Government of Region Three. Page 12

መ ቅ ድ ም ፣

በክልል ሦስት ውስጥ የሚገኙት ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለእያሌ ዘመናት በአፍ ነጻነት በተግባር ግን ፍትህና ዳኝነት በተጓደለበት ሥርዓት ተረግጠው በመገዛታቸው ምክንያት ከፍተኛ በደል የደረሰ መሆኑን በመረዳት፤

በተለይ ባለፉት 17 ዓመታት የደርግ ኢሠፓ መንግሥት የሕዝቦችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በመድፈር፤ከሕግ ውጭ በዳኝነት ሥራ የራሱን ጥቅም አስጠባቂዎች በመመደብ፤ አስተዳደራዊ ተጽእኖና በቀጥታ በመንግሥት ባለሥልጣኖች ትዕዛዝ ውሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ ፍትህ የተጓደለበት የዳኝነት አሰጣጥ መፈጠሩን በመገንዘብ

Introduction

Whereas understanding that a lot of harm had befallen on the nation-/nationalities and peoples inhabiting Region Three as they have been suppressed under the rule of oppression in a system where for many years there was freedom in words but justice and law were practically absent;

Whereas realizing that judicial function full of injustice was created especially in the last seventeen years of the Derg/WPE's regime by violating human and democratic rights of the peoples, by illegally assigning judges to serve its own interests, by imposing administrative pressure and by passing decisions at the command of authorities;

የፍትህ መጓደል የክልሉን ህብረተሰብ ሁለገብ እንቅስቃሴና ግንኙነት በብርቱ የጐዳው ሆኖ በመገኘቱና በዚህ መሠረት የቆዛባውን የፍትህ ዳኝነት አስተዳደር ሙሉ በሙሉ አፍርሶ በአዲስና ለሕዝቦች በሚጠቅም አኳኋን በማደራጀት የፍትሕን አሰጣጥ ሕጋዊ አፈጻጸም ሥርዓት ማስያዝና ከማናቸውም ዓይነት ተጽእኖ ነጻ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

በብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድር ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቍጥር 7/1984 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ሕግ ለማውጣት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር ምክር ቤት ለሽግግሩ ዘመን የፍትሕ አስተዳደር የሚበጀውን የዳኝነት አካል እንደሚከተለው አውጇል ።

ክፍል 1

አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ ፤

ይህ አዋጅ « የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቍጥር 3/85 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

አንቀጽ 2. ትርጓሜ ፤

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፤ በዚህ ዐዋጅ ውስጥ ፤

1. « ማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት » ማለት የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ማለት ነው ።

2. « ቻርተር » ማለት ሐምሌ 15 ቀን 1983 ዓ/ም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ 50ኛ አመት ቍጥር 1 የታወጀው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ማለት ነው ።

3. « የክልል ሦስት ሕዝብ » ማለት በክልል

Whereas it has been found that the miscarriage of justice has largely hampered the overall activity and relationship of the Region's society and for this it has been necessary to completely dismantle this unjust judicial administration and to systematize the legal applicability of judicial function making it independent of all kinds of pressure by reorganizing it in a manner which is new and which would serve the interest of the peoples;

Now, therefore, in accordance with the authority vested in it to promulgate proclamations by article 9 sub-article 1 of the proclamation to Provide for the Establishment of National/Regional Self-Governments, Proclamation No. 7/1992, the Council of the Transitional Government of Region Three has hereby proclaimed the following judicial body which is useful for the judicial function during the transitional period.

PART ONE

Article 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Proclamation to Establish the Courts of the Transitional Government of Region Three, Proclamation No. 3/1993.

Article 2. Definitions

In this proclamation, unless the context requires otherwise:

1. "Central Transitional Government" means the Transitional Government of Ethiopia.

2. "Charter" means the Transitional period Charter of Ethiopia proclaimed on july 23,1992 in the "Negarit Gazeta" of the 50th year, No. 1.

3. "Peoples of Region Three " means

ሦስት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 በተመለከተው ክልል የሚገኘውን ሕዝብ ማለት ነው ።

4. «የክልሉ ፍ/ቤቶች» ማለት በክልል ሦስት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 10 መሠረት የሚቋቋም ነው ።

አንቀጽ 3. <u>አ ላ ማ ፤</u>

1. በቻርተሩ ፤ በክልሉ ሕገ-መንግሥትና እንዲሁም በሌሎች ሕጐች የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብቶችና የነፃነት ጥቅሞች ማስከበር ።

2. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት ተጠብቆ ፍትህና ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲሰፍን ማድረግ ፤

አንቀጽ 4. <u>መ ቋ ቋ ም ፤</u>

ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም በወጣው ዐዋጅ ቍጥር 7/1984 የተደነገገውን መነሻ በማድረግ በክልል ሦስት ሕገ-መንግሥት ፤ አንቀጽ 27 ቍጥር 10 መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር ፍ/ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል ።

1. የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር የበላይ ፍርድ ቤት ፤ ከዚህ በኋላ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እየተባለ የሚጠቀሰው ነው ።

2. በክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር የዞን ፍ/ቤት ከዚህ በኋላ ከፍተኛ ፍ/ቤት እየተባለ የሚጠቀሰው ነው ።

3. በክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር የወረዳ ፍ/ቤት ፤ ከዚህ በኋላ የወረዳ ፍ/ቤት እየተባለ የሚጠቀሰው ነው ።

አንቀጽ 5. <u>የክልሉ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ፤</u>

በዚህ አዋጅ የክልል ፍ/ቤቶች እርከን እንደሚከተለው ተዋቅሯል ።

5.1 ጠቅላይ ፍ/ቤት ፤ አንድ ፕሬዚዳንት ፤ ሰብሳቢ ዳኛና ዳኞች ይኖሩታል ።

those peoples which inhabit the area specified by article 2, sub-articles 4 and 5 of the Region's constitution.

4."Region's Courts " means the courts to be established in accordance with article 27 sub-article 10 of the Region Three Constitution.

Article 3. <u>Objectives</u>

1. To protect the human rights and freedoms that are guaranteed by the Charter, the Region's Constitution and other laws.

2. To ensure the maintenance of law and order and the prevalence of peace and justice.

Article 4. <u>Establishment</u>

Pursuant to the provisions of proclamation No. 7/1992, the proclamation to provide for the Establishment of National /Regional Self-Governments and in accordance with article 27 sub-article 10 of the Region's Constitution the following courts of the Transitional Government of Region Three are hereby established:

1.The highest court of the Transitional Government of Region Three is hereafter called the "Supreme Court".

2.The Zonal Court of the Transitional Government of Region Three is hereafter called the "High Court".

3. The Wereda Court of the Transitional Government of Region Three is hereafter called the "Wereda Court".

Article 5. <u>Organizational Set Up</u>

In this proclamation, the hierarchy of the courts shall be as follows:

5.1 The Supreme Court shall have a president, a presiding judge and judges.

5.2 ከፍተኛ ፍ/ቤቶች፣ ሰብሳቢ ዳኞችና ዳኞች እንዲሁም ለሰባቱም ከፍ/ፍ/ቤቶች አንድ ፕሬዚዳንትና አንድ ም/ፕሬዚዳንት ይኖሯቸዋል ።

5.3 የወረዳ ፍ/ቤት አንድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ዳኞች ይኖሩታል ።

5.4 ማንኛውም ፍ/ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል ።

አንቀጽ 6. የዳኝነት ሥልጣን፣

1. የክልል መስተዳድሩ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍ/ቤቶች ብቻ ነው ።

2. የክልሉ ፍ/ቤቶች በግልጽ ተለይተው ከማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ፍ/ቤቶች ሥልጣን ስር ከሆኑት ጉዳዮች በስተቀር በሌሎች በማንኛውም የክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ ፍ/ቤቶች በማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት የዳኝነት ሥልጣን ስር የሆኑትን ጉዳዮች እንዲያዩ የውክልና ሥልጣን ሊቀበሉ ይችላሉ ።

4. የክልሉ ፍ/ቤቶች በክልሉ ውስጥ ከቻርተሩ ወይም ከክልሉ ሕገ-መንግሥት ጋር የሚጻረርን አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ትዕዛዝ የመሻር ሥልጣን አላቸው ።

አንቀጽ 7. ችሎት፣

1. ማንኛውም ፍ/ቤት አንድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ የሆኑ ችሎቶች ይኖሩታል ።

2. በእያንዳንዱ የጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ ።

3. የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ማናቸውንም የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንትም ማናቸውንም የከፍተኛ ፍ/ቤት ችሎት ሊሰበስቡ ይችላሉ ።

4. የከፍተኛው ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬ

5.2 The High Courts shall have presiding judges, judges as well as a president and a vice president for the seven High Courts.

5.3 The Wereda Court shall have one or when necessary, more judges.

5.4 Each court shall have the necessary support staff.

Article 6. Judicial Power

1. The judicial power of the Regional Government shall be vested only in the Region's Courts.

2. Excepting the cases which are within the jurisdiction of the Supreme Court of the Central Transitional Government all other cases internal to the Region are within the jurisdiction of the Region's Courts.

3. Notwithstanding to sub-article 2 of this article the Region's Courts when delegated may entertain cases which are within the jurisdiction of the Courts of the Central Transitional Government.

4. The Region's courts shall have power to repeal any administrative measure or order in the Region that contradicts with the Charter, or the Region's Constitution.

Article 7. Divisions

1. There shall be one or more divisions in a court.

2. In each division of the Supreme Court and the High Court there shall be one presiding judge and two other judges.

3. The president of the Supreme Court, the president and the vice-president of the High Courts may preside over any division in their respective courts.

4. The president and vice president of the High Courts may sit in a

ዚዳንት በጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት ዳኛ ሲጎድል እሟልተው ያስችላሉ ።

5. የወረዳ ፍ/ቤት ችሎት በአንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ዳኞች ያስችላል ።

አንቀጽ 8. <u>የማስቻያ ስፍራ</u>፤

1. የጠቅላይ ፍ/ቤት ማስቻያ ስፍራ የክልሉ ዋና ከተማ ይሆናል ።

2. የከፍተኛው ፍ/ቤት ማስቻያ ስፍራ የዞኑ ዋና ከተማ ይሆናል ።

3. የወረዳው ፍ/ቤት በወረዳው ዋና ከተማ ያስችላል ።

4. በየትኛውም እርከን ላይ ያለ የክልል ፍ/ቤት ፍትሐዊ አስተዳደር ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ዳኞችን በመላክ በሥልጣኑ ክልል ውስጥ በማንኛውም ስፍራ ያስችላል ።

አንቀጽ 9. <u>በግልጽ ችሎት ስለማስቻል</u>፤

1. ማንኛውንም ጉዳይ ዳኞች በግልጽ ችሎት ያስችላሉ ።

2. በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ለዳኝነት አሰራር አግባብ ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕጐች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ዳኞች በዝግ ያስችላሉ ።

2.1 ለሕዝብ ሰላምና ፀጥታ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ወይም፤

2.2 ለሕዝብ መልካም ባህልና ሥነ-ምግባር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፤

አንቀጽ 10. <u>ውሳኔ አሰጣጥ</u>፤

1. ሦስት ዳኞች ሆነው በሚያስችሉበት ችሎት ዳኞች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ልዩነት ካላቸው የአብዛኛው ድምጽ ውሳኔ የፍ/ቤቱ ውሳኔ ይሆናል ።

2. የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በመዝገቡ መስፈር ይኖርበታል ።

አንቀጽ 11. <u>ከችሎት ስለመነሳት</u>፤

1. የማንኛውም ፍ/ቤት ዳኛ አንድን ጉዳይ

supreme court division when the division faces shortage of judges.

5. A case in the Wereda Court may be heard by one or more judges.

Article 8. <u>Place Of Sitting</u>

1. The place of sitting of the Supreme Court shall be the Region's capital.

2. The place of sitting of the High Court shall be the capital of the Zone.

3. The place of sitting of the Wereda Court shall be the capital of the Wereda.

4. Where a court at any level finds it necessary, it may hold circuit hearings in any other place within the area designated for its jurisdiction.

Article 9. <u>Open Hearings</u>

1. Judges shall hear every case in open court.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this article and without prejudice to other relevant procedural laws, judges may hear cases in camera where such proceedings are necessary for:

1. public peace and security; and

2. people's valuable culture and morality.

Article 10. <u>Disposition of Judgement</u>

1. Where a case is heard by three judges decisions shall be adopted by majority.

2. The descenting opinion shall be registered in the file.

Article 11. <u>Prohibition</u>

1. Any judge prohibited by law not

እንዳያይ በሕግ የተከለከለ ከሆነ ጉዳዩን ማየት አይችልም ።

2. አንድ ዳኛ አንድን ጉዳይ ማየት አይገባውም በማለት ከችሎት እንዲነሳ በሚጠየቅበት ጊዜ አፈጻጸሙ በሕግ በተወሰነው መሠረት ይሆናል ።

አንቀጽ 12. <u>የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ ፤</u>

1. የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 48 መሠረት የክልሉ የሥራ ቋንቋ ነው ።

2. ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ ለማይችል ባለ ጉዳይ አስተርጓሚ ይመድቡለታል ፤ ወይም ራሱ አስተርጓሚ ይዞ ሊቀርብ ይችላል ።

3. የወረዳ ፍ/ቤቶች የሥራ ቋንቋ በአዋጅ ቁጥር 7/84 ለወረዳዎች በተሰጠው መብት መሠረት ይከናወናል ።

አንቀጽ 13. <u>የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ፤</u>

እስከ አሁን እየተሠራባቸው ያሉት የፍትሐ-ብሔርና የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጎች እንዲሁም ሌሎች ሕጎች ጭምር ከአስፈላጊ ማሻሻያ ጋር ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የሥልጣን ክልል ፤</u>

አንቀጽ 14. <u>ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፤</u>

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚከተለው የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ።

1. ከከፍተኛው ፍ/ቤቶች የሚቀርቡለትን የይግባኝ አቤቱታዎች እየተቀበለ ይወስናል ። ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል ።

2. በክልሉ ሕገ-መንግሥትና በሌሎችም የምክር ቤቱ ሕጎች ላይ በሚነሱ የሕግ ክርክሮች የሕግ ትርጉም የመስጠት የመጨረሻ ሥልጣን ይኖረዋል ።

to hear a case may not sit in the proceedings of the case.

2. when an application for the removal of a judge from a case is submitted the making of a decision on the challenge shall be as stipulated by law.

Article 12. <u>Working Language of the Courts</u>

1. The working language of the courts shall be the working language of the Region as stipulated in article 48 of the Region's Constitution.

2. The court shall provide an interpreter to a party who does not understand the working language, or the party may bring one.

3.The working language of the Wereda Court shall be decided in accordance with the right given to the weredas in proclamation No. 7/1992.

Article 13. <u>Procedural Laws</u>

The Civil Procedure Code and the Criminal Procedure Code that are presently in effect as well as the other laws shall remain applicable along with the amendments.

PART TWO

<u>SCOPE OF JUDICIAL POWER</u>

Article 14. <u>The Supreme Court</u>

The Supreme Court of the Region shall have the following judicial powers:

1. It shall have an appellate jurisdiction over cases that come from the High Courts; and its decisions shall be final.

2. It shall be in its power to give final interpretation in legal disputes emanating from the Regional Constitution and other laws passed by the Council.

23

3. በክልሉ ውስጥ የዳኝነት አሰራርን ለማሻሻል እና ለማዳበር እንደ አስፈላጊነቱ ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን ይሰጣል ።

አንቀጽ 15. <u>ከፍተኛ ፍ/ቤት ፤</u>

ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚከተለው የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ።

1. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 በማይፃረር መንገድ በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጐች ውስጥ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያያቸው የተሰጡትን ጉዳዮች ይመለከታል ።

2. ከወረዳ ፍ/ቤት በይግባኝ በሚቀርቡለት ጉዳዮች ላይ ይወስናል ።

አንቀጽ 16. <u>ወረዳ ፍ/ቤት ፤</u>

የክልሉ ወረዳ ፍ/ቤት በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጐች ውስጥ ለአውራጃና በወረዳ ፍ/ቤቶች እንዲታዩ የተዘረዘሩትንና ከቀበሌ የፍርድ ኮሚቴዎች በይግባኝ የሚተላለፉለትን ጉዳዮች የማየት ሥልጣን ይኖረዋል ።

<u>ክፍል ሦስት ፤</u>

<u>ስለ ዳኞች ፤</u>

አንቀጽ 17. <u>ለዳኝነት ሙያ የሚያበቁ መመዘኛዎች ፤</u>

በማንኛውም የፍርድ ቤቶች እርከን ለዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ መመዘኛዎች ፤

1. ለቻርተሩ ፤ ለክልሉ ሕገ መንግሥት እና ለሌሎችም ሕጐች ታማኝ መሆን ፤

2. በሕግ ትምህርት የሰለጠነ ወይም በልምድ በቂ የሕግ ዕውቀት ያለው መሆን ፤

3. በታታሪነቱ ፤ በታማኝነቱ ፤ በሕዝባዊ ወገንተኝነቱ ፤ በፍትሐዊነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ ፤ መሆን ፤

4. በዳኝነት ሙያ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን ፤

3. It issues orders and directives to improve and strengthen judicial function in the Region.

Article 15. <u>The High Court</u>

The High Court shall have the following judicial powers:

1. Without contradiction to article 6 sub-article 2 of this proclamation it shall have jurisdiction over cases assigned to the High Court in the Ethiopian Civil and Criminal Procedure laws.

2. It shall have an appellate jurisdiction over cases that come from the Wereda Court.

Article 16. <u>The Wereda Court</u>

The wereda courts of the Region shall have jurisdiction over cases which were assigned to the Awraja and Wereda Courts in the Ethiopian Civil and Criminal Procedure laws and an appellate jurisdiction over cases which come from Kebele Judicial committees.

PART THREE

<u>The Judges</u>

Article 17. <u>Criteria for Becoming a Judge</u>

To be selected as a judge at any court level a person shall;

1. be committed to the Charter, the Regional Constitution and the other laws.

2. have sufficient legal training or acquire broad legal skill through experience.

3. have a good reputation for his credibility, diligence, partisanship to the people, sense of justice and conduct.

4. be willing to work as a judge.

በጎንደር ማተሚያ ቤት ታተመ
PRINTED B[...] PRINTING PRESS

5 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 መሰረት ለዳኝነት ሥራ ያልተከለከለ መሆን ናቸው ።

አንቀጽ 18. ዳኞች እንዳይሆኑ የተከለከሉ ፤

1. የኢ.ሠ.ፓ አባል የነበረ ፤

2. በደርግ ኢ.ሠ.ፓ መንግሥት በደኅንነት ሥራ ተሰማርቶ የነበረ ፤

3. በደርግ ኢ.ሠ.ፓ መንግሥት በፖለቲካ፤በጦር ኃይሎች እንዲሁም በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበረ፤ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ።

4. ፖለቲካ ነክ ባልሆነ ወንጀል ተከሶ የእስራት ፍርድ የተፈረደበት ፤

አንቀጽ 19. የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አሿሿም ፤

1. የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ዳኞች፤የከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች በክልሉ ም/ቤት ሊቀመንበር አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማሉ ።

2. የወረዳው ፍ/ቤት ዳኞች በወረዳው ም/ቤት ሊ/መንበር አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማሉ ።

አንቀጽ 20. ዳኞች ከሥራቸው እንዲነሱ ስለማድረግ ፤

1. ከጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት በስተቀር ማንኛውም ዳኛ የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት ከዳኝነት ሊነሳ የሚችለው ከዳኝነት ሥራ የሚያስነሳ ጥፋት ለመፈፀሙ በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሲረጋገጥ ነው ።

2. የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ዳኞች ፤ የከፍተኛው ፍ/ቤት ፤ ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት የሥራ ዘመናቸው ከማለቁ በፊት በቂ ምክንያት ሲኖር በሾማቸው የክልሉ ም/ቤት ሊነሱ ይችላሉ ።

3. የከፍተኛውን ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፤ ም/ፕሬዚዳንትና ዳኞች ከዳኝነት ሥራ የሚያሰግዳቸው ተግባር

5. be one who is not prohibited from being a judge in accordance with article 18 of this proclamation.

Article 18. Persons Prohibited from Being Judges

1. WPE member;

2. One who was engaged in security activities in the Derg/WPE regime;

3. One who held high position in the political establishment, in the armed and police forces in the Derg/WPE regime, the details of which shall be decided by law.

4. One who was charged and convicted with non-political criminal offenses.

Article 19. Appointment Procedure

1. The president and the judges of the Supreme Court, the president, vice-president and the judges of the High courts shall be appointed by the Regional Council upon the recommendation of the chairman of the Council.

2. The judges of the Wereda Courts shall be appointed by the council upon the recommendation of the chairman of the Wereda Council.

Article 20. Termination of Tenure

1. With the exception of the president of the Supreme Court, any judge may be discharged from duty before his /her term of office ends, provided that the Judicial Commission proves that he/she is guilty of judicial work.

2. The president and judges of the Supreme Court, and the president and vice-president of the High Courts may be discharged from duty by the Regional Council which appointed them, before their term of office ends when it finds sufficient reason to do so.

3. When an activity that enforces termination of tenure which has been

ሲኖርና ይህም በዳኞች የአስተዳደር ጉባኤ ሲረጋገጥ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እስከ ም/ቤቱ ስብሰባ ድረስ አግዶ ሊያቆያቸው ይችላል ።

4. በወረዳ ምክር ቤት የተሾሙ ዳኞች ፤የሥራ ዘመናቸው ከማለቁ በፊት በቂ ምክንያት ሲኖር በሾማቸው ምክር ቤት ሊነሱ ይችላሉ ። ሆኖም የወረዳ ፍ/ቤት ዳኞች ከዳኝነት ሥራ የሚያሳግዳቸው ተግባር ሲኖርና ይህም በዳኞች የአስተዳደር ጉባኤ ሲረጋገጥ የወረዳው ም/ቤት እስኪሰበሰብ የወረዳው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከዳኝነት ሥራ አግዶ ሊያቆያቸው ይችላል ።

አንቀጽ 21. <u>የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር ፡</u>

<u>የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ፤</u>

1. በሕጉ መሠረት ፍ/ቤቱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት ፤
2. ፍ/ቤቱን ይወክላል ፤
3. የፍ/ቤቱን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ።
4. የክልሉን ዳኞችና ሬጅስትራሮች በሙያቸው ይደለድላል ፤ ያስተዳድራል ።
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶችን የማስቻያ ስፍራ ይወስናል ።
6. ወንጀልን ለመከላከልና የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር ከክልሉ የፍትህ ቢሮና ከዐቃቤ ሕግ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በመመካከር ይሠራል ።
7. ትምህርታዊ የሆኑ የየዓመቱ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው እንዲታተሙ ያደርጋል ።

proved by the Judicial Commission takes place, the president the vice-president and the judges of the High Courts may be suspended from duty by the Executive Committee of the Region until the general assembly of the Regional Council is called.

4. Judges appointed by the Wereda Council may be discharged from duty before their term of office ends by the council that appointed them if it finds sufficient reason to do so. However, when the judges of the Wereda Courts are found in activities that may result in termination of tenure and when that is proved by the Judicial Commission the Wereda Executive Committee may suspend them until the general assembly of the Wereda Council.

Article 21. <u>Powers and Duties of the President of the Supreme Court</u>

The president of the Supreme Court shall:

1. Administer the Court in accordance with the law.
2. Represent the Court.
3. Prepare and submit the work programme and budget of the Court; and implement same upon approval.
4. Assign and administer judges and registrars of the Region.
5. Decide the place of sitting of the Supreme Court pursuant to article 8 sub-article 4 of this proclamation.
6 Work in consultation with the heads of the Regional justice bureau and the attorney office in order to prevent crimes and strengthen judicial function.
7. Publish selective and educative judgements yearly.

8. የጠቅላይ ፍ/ቤት የሕግ መጽሔት እንዲዘጋጅ ያደርጋል ።

9. በክልሉ ውስጥ ስላሉ ፍ/ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴ ለክልሉ ም/ቤትና ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በየሦስት ወሩ ዘገባ ያቀርባል ።

10. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለክልሉ ም/ቤት ነው ።

11. በዚህ እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል።

አንቀጽ 22. <u>የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንት ፤</u>

የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ሆኖ ፦

1. በሕጉ መሰረት ፍርድ ቤቶችን ያስተዳድራል ።
2. የከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን ይወክላል ።
3. የፍርድ ቤቶችን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ።
4. የከፍተኛ ፍ/ቤቶችን ዳኞች ይደለድላል ።
5. በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የከፍተኛ ፍ/ቤቶችን የማስቻያ ስፍራ ይወስናል ።
6. የየአመቱን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምርጥ ፍርዶች ለጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲላኩ ያደርጋል ።
7. ስለከፍተኛ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራ እጠቃላይ እንቅስቃሴ በየሦስት ወሩ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ዘገባ ያቀርባል ።
8. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ችሎት በጉደለ ጊዜ አሟልቶ ያስችላል ።
9. ወንጀልን ለመከላከልና የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር ከዞኑ የፍትሕ አካልና ከአቃቤ ሕግ መ/ቤት

8. Publish a law journal of the Supreme Court.

9. Submit a report on the judicial activities of the courts in the Region to the Regional Council and the Executive Committee of the Regional Council every three months.

10. Be accountable to the Regional Council.

11. Perform duties entrusted to him by this proclamation and other laws.

Article 22. <u>The President of the High Courts</u>

The accountability of the president of the High Courts being to the Regional Supreme Court, he/she:

1. shall administer the High Court in accordance with the law.
2. shall represent the High Courts.
3. shall submit the work program and budget of the Court, and implement same upon approval.
4. shall assign the judges of the High Courts.
5. shall decide the place of sitting of the High Courts pursuant to article 8, sub-article 4.
6. shall submit to the Supreme Court selective judgements of the High Courts of every year.
7. shall submit to the president of the Supreme Court, reports on general judicial activities of the High Courts every three months.
8. may sit in any division of the Regional Supreme Court when the need arises.
9. shall work in consultation with the heads of the zonal justice organs and attorney offices in order to

ኃላፊዎች ጋር በመመካከር ይሰራል ።

10. በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

አንቀጽ 23. <u>የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ም/ፕሬዚዳንት ፤</u>

የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ም/ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለከፍተኛው ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንት ሆኖ ፤

1. የከፍተኛው ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት በሌለ ጊዜ ወይም ሥራውን ሊሠራ በማይችልበት ወቅት ተክቶ ይሠራል ።

2. ሌሎች በከፍተኛው ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል ።

አንቀጽ 24. <u>የወረዳ ፍ/ቤት ሰብሳቢ ዳኛ ፤</u>

የወረዳ ፍ/ቤት ሰብሳቢ ዳኛ ተጠሪነቱ ለከፍተኛ ፍ/ቤትና ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ ፤

1. በሕጉ መሠረት ፍ/ቤቱን ያስተዳድራል ።

2. የወረዳ ፍ/ቤቱን ይወክላል ።

3. የፍ/ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል ።

4. የፍ/ቤቱን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ።

5. የፍ/ቤቱን ዳኞች ይደለድላል ።

6. ስለፍ/ቤቱ ሥራ እንቅስቃሴ በየሦስት ወሩ ለከፍተኛው ፍ/ቤትና ለወረዳው ም/ቤት ዘገባ ያቀርባል ።

7. በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ፤ በጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና በከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል ።

prevent crime and strengthen judicial function.

10. shall perform duties entrusted to him/her by this proclamation and other laws.

Article 23. <u>The vice-president of the High Courts</u>

The accountability of the vice-president of the High Courts being to the president of the High Courts, he/she:

1. shall serve as acting president when the president of the High Courts is absent or is unable to perform his/her duties.

2. shall discharge duties to be assigned to him/her by the president of the High Courts.

Article 24. <u>Presiding Judge of the Wereda Court</u>

The accountability of the presiding judge of the Wereda Court being to the High Court and the Wereda Council, he/she shall;

1. administer the court in accordance with the law.

2. represent the Wereda Court.

3. administer employees of the court.

4. submit the work program and budget of the court, and implement same upon approval.

5. assign the judges of the court.

6. submit to the High Court and the Wereda Council reports on the activities of the Court every three months.

7. implement directives issued by the Judicial Commission, the president of the Supreme Court and the president of the High Courts.

8. ወንጀልን ለመከላከልና የዳኝነት ሥራን ለማ ጠናከር ከወረዳው የፍትሕና የዐቃቤ ሕግ ተጠሪ ጋር በመመካከር ይሰራል ።

9. በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

ክፍል አራት፡

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 25. ዳኞች በዳኝነት ሥራ ላይ ነጻ ስለመሆና ቸው፡

ዳኞች በዳኝነት ሥራ ላይ ነጻ ናቸው ፣ ከሕግ በቀር በሌላ አካል አይመሩም ።

አንቀጽ 26. ተጠያቂነት፡

ማንኛውም ዳኛ የሙያው ሥነ ምግባር ከሚያዘው ውጭ ከፈጸመ በሕግ ፊት ተጠያቂ ነው ።

አንቀጽ 27. የፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መከበር፡

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸውን ሕጋዊ ውሳኔዎችና ትዕዛዞች ግለሰብ ፣ ድርጅትም ሆነ መንግሥታዊ አካል የማክበር ግዴታ አለበት ።

አንቀጽ 28. ቃለ መሐላ፡

ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ ።

አንቀጽ 29. አዋጁን ስለማሻሻል፡

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ሊሻሻል ይችላል ።

አንቀጽ 30. የተሻሩ ሕጎች፡

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

አንቀጽ 31. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በዝክረ ሕግ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

ሰኔ 18 ቀን 1985 ዓ/ም

አዲሱ ለገሰ
የክልል ሦስት ምክር ቤት
ሊቀመንበር
ባሕር ዳር

8. work in consultation with representatives of the wereda Justice organ and attorney offices in order to prevent crime and strengthen judicial function.

9. perform duties entrusted to him/her by this proclamation and other laws.

PART FOUR

Miscellaneous Provisions

Article 25. Independence of the Judiciary

Judges shall be independent in the discharge of their judicial function; they shall be guided by nobody other than the law.

Article 26. Responsibility

Any judge is answerable for any of his activities which does not conform to his professional ethics.

Article 27. Execution and Implementation of Court Orders

Every individual, organization or government organ shall respect the legal decisions and orders passed by the Region's Courts.

Article 28. Oath

Judges shall be sworn in before starting their duty.

Article 29. Amendment

This proclamation may be amended by the Regional Council.

Article 30. Repealed Laws

Any law inconsistent with this proclamation shall be inapplicable with regard to matters provided for in this proclamation.

Article 31. Effective Date

This proclamation shall come into force on the date of its publication in the Zikre Hig.

25th June, 1993
Addisu Legesse
Chairman of the Council of
Region 3
Bahir Dar